# በልማትና በበዓለ ልደት ስም የአካባቢያችን ነጭ አሞራዎች ንቅዘት

የስመ የካቲት 11 እና የአባይ ግድብ ልማት በሚል ሽፋን ሕብረተሰቡን ዳግም ለማሞኘትና ለማወናበድ የነጭ ቁራ መልክተኞች ሲቅበዘበዙ በይፋ እየታየ ነው።

የነጭ አሞራ ሃዋርያት ከጉያችን ውስጥ ሁነው ለፋሽስት መንግስት ተብያቸው የውጭ ምንዛሪ ማሚያ እንዲሆን በልማትና በበዓለ ልደት ስም ወደኪሳችን ለመግባት መርዝ እንደበላ ውሻ በመንቀዥቀዥ ላይ ይገኛሉ። እረ ለመሆኑ መቼ ነው እኛ ኢትዮጵያውያን እራሳችንንን አውቀን አገርና ሕዝብን ከመበደል ይልቅ ለአገራችንና ለሕዝባችን ጋሻ መከታው ሁነን የምንቆመው? እስከመቼስ ነው በራሳችን ፍቃደኛነት ህሊናችንን ለንዋይ ሸጠን፣ ውድ ወገናችን ክደንና አዋርደን በጥፋትና በፍልሰት ሰንሰለት የፌጥኝ ታስረን የምንቀጥለው?።

ማስተዋልና ማመዛዘን የጎደለን ትምክህተኞች፣ መንደርተኞች፣ ውሸተኞችና አስመሳዮች አገራችንንና ሕዝባችንን ጎጂ የሆኑ ተግባሮችን በጥቃቅን ጥቅም በመደለል በስራ ላይ ለማዋል እንቅልፍ አጥተን ሌት ተቀን የምንሯሯጠው? ቆም ብለንስ ከህሊናችን ጋር በመታረቅ ምን እያደረግን ነው ብለን እራሳችንን በመጠየቅ ያበላሸውን ለማስተካከል የማንሞክረው? ለአለፉት ሃያ ዓመታት በሕዝብ ስልጣን ኮርቻ ላይ በማን አለብኝነት ተንፈራጦ በመቀመጥ አገርና ሕዝብን እያሰቃየ ያለው መንግስት ተብዬ ድርጅት በደደቢት በረሃ ላይ የተመሰረተበትን የካቲት 11ቀን 1967 ዓመተ ምህረት እንደ ሕዝብ በዓል ለማክበር በያካባቢው የምንገኝ የነጭ አሞራ ሃዋርያት ዛሬም እንደትላንቱ ሕዝብና አገርን በመበደል አለቆቻችንን ለማስደሰትና ፍርፋሪ ለመልቀም ስንሯሯጥ መታየታችን እጅግ በጣም አሳፋሪና አሳዛኝ ከመሆኑም በላይ ስብእናችንን ለጥቅም አሳልፈን የሸጥን የዘመኑ ከሃዲ ባንዳዎች መሆናችንን ኢትዮጵያዊው ሕብረተሰብ ከተገነዘበው ውሎ ማደሩና በሕብረተሰቡ ውስጥ ተሸማቀንና አንገታችንን ደፍተን መታየታየታችን የቁም ሞት መሆኑን መመመልከት አለመቻላችን ነው።

በከተማችን ውስጥ የኢሕአዴግ መንግስት የሚቆጣጠረው ወይም የኔ ነው የሚለው አንድም ነገር የለም። ይህም የሚያሳየው ባለፈው ዓመት የካቲት 11 በ36ኛው የልደት በዓል በተከበረበት ወቅት በቦታው ተገኝተው የነበሩት በጥቂት የትግራይ ማሕበረሰብ ብቻ ሲሆኑ ቀሪው ኢትዮጵያዊ ማሕበረሰብ የዚህ ፊንጠዝያ ተካፋይ አልነበረም። ሆኖም ግን በዓሉን ያዘጋጁት የትግራይ ማሕበረሰብ መሪዎች ነን ባዮች የመንግስቱ ቡችሎች ሃገራዊ በዓል አስመስለው በማቅረብ ሞክረው ነበር። ነገር ግን በዚህ ከተማ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ማሕበረሰብ በዘርና በጎሳ ሳይለያይ የአገርንና የሕዝብን ጥቅም ከሚያስጠብቁ ሃይሎች ጋር በመሰባሰብ በቅርበት የሚሰራ በመሆኑ ለነዚህ አድር ባዮች የውስጥ እግር እሳት ከመሆኑም በላይ ለበሬ ወለደ ውሸታቸውና ቅጥፈታቸው መፈናፈኛ አሳጥቷቸዋል። እነዚህ አድር ባዮች ይህንንም በማወቃቸው አለቆቻቸው ወደ ከተማችን ብቅ ሲሉ ወግ አይቀርምና አደረግን ብለው ለሚለፍፉት “ሕዝባዊ” ስብሰባ እራቅ ካለ ቦታ የቅርብ ዘመዶቻቸውን፣ የጥቅም ተጋሪና በጣት የሚቆጠሩ ደጋፊዎቻቸውን በማጓጓዝ በአካባቢው ድጋፍ እናዳላቸው ለማሳየት ሲሞክሩ በተደጋጋሚ ታይተዋል።

አገራችን በአኩሪ ታሪኳና በጀግናው ሕዝቧ በመላው ዓለም ተከብራ ለሌሎችም እንደ ምሳሌ እየተነገረች የቆየች መሆኑዋ ለሁሉም የሚያውቀው ሃቅ ነው። ይህንን አኩሪ ታሪካዊ ሃቅ ተቀብሎ ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅም አኩሪ ስራን መስራት በትውልድ የሚያስመሰግንና ለራስም የአእምሮ እርካታን የሚሰጥ በመሆኑ ባሁኔ ሰዓት ለም መሬታችንን ለባእዳን እየቸበቸበ፣ ሕዝብን ከሕዝብ እያጋጨ ተቃዋሚውን ለእስርና እንግልት እየዳረገ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ለሚሰራ ስርዓት መጎናበሱን ትተን ከሰፊው ሕዝብ ጋር በመቆም እንደ አጀግና አባቶቻችን የዜግነት ግዴታችንን መወጣት ይገባናል። ጥቂት በስልጣን የሰከሩና በገንዘብ ባሕር ውስጥ ለሚዋኙ ግለሰቦች ጥቅም ብለን በራሳችን ቤተሰብ ላይ ሊደርስ የማንፈልገውን በደል በወገናችን ላይ ለማድረስ ከመቅነዝነዝ እንቆጠብ። ይህንን ማድረግ ካልቻልን የምልዓተ ኢትዮጵያ ሕዝብ ልሳን ፊፅሞ የማይታገት እሳተ መለኮታዊ ነበልባል ነውና በእሳቱ ከመንደድ እራሳችንን እናድን።

ፅንዓት ለኢትዮጵያ ሕዝብ
ከሕሉፍ በርሄ